

# ፆም እንደጋሻ

## የረመዳን ሕጎቹና ደንቦቹ ከነጥያቄና መልሶቹ

ከሙንተቃ ፈታዋ አል ሼኽ ፈውዛን

እና

ከሰሒሕ ፊቅሂ-ሱና በሰይድ ሳሊም ኪታቦች የተወሰደ

አዘጋጅና ትርጉም - ሰይፈዲን ሐበሻ
ከጅዳ የኢትዮጵያዊያኖች የዳዕዋ ማዕከል

1426 ዓመተ ሂጅራ
1427

# ማውጫ


| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|
| 1ኛ - መግቢያ ............................................................ | 4 |
| 2ኛ - ስለፆም ማብራሪያ ...................................................... | 5 |
| 3ኛ - የፆም ደረጃውና ጥቅሙ ............................................. | 5 |
| 4ኛ - የፆም አይነቶች ሁለት ናቸው....................................... | 6 |
| 5ኛ - የረመዳን ፆም ሕግ (ሑክም) ...................................... | 7 |
| 6ኛ - የረመዳን ወር መግባቱ ............................................... | 8 |
| 7ኛ - የረመዳን ጨረቃ (ሂላል) ............................................ | 9 |
| 8ኛ ትክክለኛ ፆም ......................................................... | 10 |
| 9ኛ - የፆም መዐዘን (ሩክን) ................................................ | 11 |
| 10ኛ - ሱሑር .............................................................. | 12 |
| 11ኛ - ሱሑርን ስለማዘግየት ............................................... | 13 |
| 12ኛ - በኢፍጣር ስለመቻኮል ............................................... | 13 |
| 13ኛ - በፊጥር ወቅት ዱዓ ማድረግ ..................................... | 14 |
| 14ኛ - ቁርአን መቅራት በረመዳን ........................................ | 14 |
| 15ኛ - የፆም ምንዳ ሚቀንሱ ............................................. | 15 |
| 16ኛ - በግልፅ ፆም የሚበላሹ ............................................. | 15 |
| 17ኛ - የፆም መበላሸት በሁለት ይከፈላል ............................... | 15 |
| 18ኛ - ፆሙ ተበላሽቶ ከፋራ የሚያስገድድ ............................. | 16 |
| 19ኛ - የፆመኛ ትጥበት በቀን ............................................ | 17 |
| 20ኛ - ፆመኛ መጉመጥመጥ ............................................... | 18 |
| 21ኛ - ፆመኛ ምግብ ስለመቅመስ ....................................... | 18 |
| 22ኛ - ዋግምት ወይንም ደም መለገስ ለፆመኛ........................ | 18 |
| 23ኛ - ፆመኛ ጥርሱን ስለመፋቅ ......................................... | 19 |
| 24ኛ - ፆመኛ አክታን ስለመዋጥ ......................................... | 19 |

*25ኛ - በምክንያት የሚያፈጥሩ ............................................... 19*

*26ኛ - የሽማግሌዎችና የአረጋዊያን ፆም ................................. 20*

*27ኛ - የእርጉዝ ሴት ፆም .................................................... 20*

*28ኛ - ሴቶች የወር አበባን የሚያቆም ኪኒን .......................... 21*

*29ኛ - በሴቶች ላይ የማያቋርጥ ደም (ኢስቲሐዳ)...................... 21*

*30ኛ - የረመዳን ቀዷ ............................................................ 21*

*31ኛ - የሸዋል ፆም .............................................................. 22*

*32ኛ - የአሹራ ፆም .............................................................. 23*

*33ኛ - ሻዕባን ወር ላይ ፆም ማብዛት ....................................... 23*

*34ኛ - የዓረፋ ቀን ፆም ......................................................... 24*

*35ኛ - የሰኞ እና የሐሙስ ፆም ................................................ 24*

*36ኛ - በየወሩ ሦስት ቀን መፆም ........................................... 24*

*37ኛ - ባለትዳር ሴት ስትፆም ባሏን ስለማስፈቀዷ .................. 24*

*38ኛ - አመቱን ሙሉ ስለመፆም ............................................ 25*

*39ኛ - ስለ ረጀብ ፆም ........................................................... 25*

*40ኛ - ለይለቱል ቀድር ........................................................... 25*

*41ኛ - አል ኢዕቲካፍ .............................................................. 25*

*42ኛ - ስለረመዳን ፆም ጥያቄና መልስ .................................. 26 - 36*

# بسم الله الرحمن الرحيم

**إن الحمد لله نحمده، ونستعينه، ونستغفره، ونعوذ بالله من شرور أنفسنا وسيئات أعمالنا، من يهده الله؛ فلا مضل له، ومن يضلل؛ فلا هادي له. وأشهد أن لا إله إلا الله وحده لا شريك له، وأشهد أن محمداً عبده ورسوله صلى الله عليه وعلى آله وصحبه وسلم.**

ምስጋና ለአላህ ስለተገባው እናመሰግነዋለን በሱም እንረዳለን ምህረትም እንከጅላለን ከነፍሶቻችን ሸሮችና ከወንጀል ሥራዎቻችን በአላህ እንጠበቃለን አላህ ቀጥተኛውን መንገድ የመራው ማንም አያጠመውም የተጣመመን ደግሞ ከአላህ በስተቀር ማንም አይመራውም:: ከአላህ በስተቀር በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባው አምላክ የለም አላህ አንድ ነው ሽርክም የለውም ነብዩ መሐመድም የአላህ አገልጋይ እና መልዕክተኛ መሆናቸውን እንመሰክራለን ሰላምና ሰላት በአላህ መልዕክተኛ በቤተሰባቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን ::

## መግቢያ

በረመዳን ፆም ዙርያ ሕጎቹንና ደንቦችን ጥያቄዎችንና መልሶቻቸውን የያዘ ዘርዘር ያለ የትርጉም ሥራ እነሆ ቀርቧል ::

ይህ ፆም እንደ ጋሻ በሚል ስያሜ ስለረመዳን ፆም መልዕክት የተውጣጣው ከሁለት ኪታቦች ሲሆን አንደኛው ከሼኽ ሷሊሕ ቢን ፈውዛን ቢን ዓብደላህ ፈውዛን በተለያየ ጊዜ የሰጡትን ፈታዋ ያሰባሰበው (አል ሙንተቃ ሚን ፈታዋ ሼኽ ፈውዛን) ከሚለው ኪታብ ሁለተኛው በሼኽ አቡ ማሊክ ከማል ቢን ሰይድ ሳሊም የተዘጋጀው (ሰሒሕ ፊቅሂ አል ሱናህ) ከሚለው ኪታብ ነው::

# ስለፆም ማብራሪያ

ፆም ማለት ትርጉሙ ከአንድ ነገር መቆጠብ ወይንም መከልከል ማለት ሲሆን ለምሳሌ አላህ በቁርአኑ ስለመርየም ሲያወሳ :-

قال تعالى: ﴿ فَكُلِي وَٱشْرَبِي وَقَرِّي عَيْنًا ۖ فَإِمَّا تَرَيِنَّ مِنَ ٱلْبَشَرِ أَحَدًا فَقُولِيٓ إِنِّي نَذَرْتُ لِلرَّحْمَٰنِ صَوْمًا فَلَنْ أُكَلِّمَ ٱلْيَوْمَ إِنسِيًّا ﴿٢٦﴾ ﴾

**ትርጉሙም ((ብይም ጠጪም ተደሰቺም ከሰዎችም አንድን ብታይ እኔ ለአል ረሕማን ዝምታን (ፆምን) ተስያለሁ ዛሬም ሰውን በፍፁም አላናግርም በይ::))**

*መርየም - 26*

እዚህ ላይ (ፆም) የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመርየምን ዝም ማለት ወይንም ከንግግር መቆጠብ ማለት ነው::

ሌላው በሸሪዓው ፆም ማለት ከፈጅር ጀምሮ ቀኑን ሙሉ ፀሃይ እስክትጠልቅ ድረስ ከምግብ ከመጠጥና ሌሎች ፆምን ከሚያገድፉ ነገሮች አላህን ለመገዛት ነይቶ መቆጠብ (መታቀብ) ማለት ነው::

# የፆም ደረጃውና ጥቅሙ

**1ኛ** - ፆም ወደ አላህ ከሚቃረቡበት ከትላልቅ የዒባዳ አይነቶች አንዱ ነው :: ሙእሚኖች በፆም ከአላህ የሚያገኙት ምንዳ ወደርና ልክ የለውም በመፆም ያለፉት ወንጀሎች ይማራሉ፣ በመፆም ፊቶች ከእሳት ይርቃሉ፣ ፆመኞች ልዩ በሆነው የጀነት በር ይገባሉ፣ ፆመኛ ጌታውን ሲገናኝ ይደሰታል::

አቡሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ባወሩት ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) « አላህ የአደም ልጆች ሥራቸው ሁሉ ለራሳቸው ነው ፆም ብቻ ሲቀር ፆም የኔ ነው ምንዳውንም የምከፍለው እኔው ነኝ አለ፣ ፆም ጋሻ ነው ከአንዳቹህ መሐል በሚፆምበት ቀን እንዳይረክስ እንዳይጮህ እንዳይሞኝም አንዱ ቢሰድበው ወይንም ቢጣላው እኔ ፆመኛ ነኝ ይበል (ሁለት ጊዜ): የመሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነው (በአላህ

እምላለሁ) የፆመኛ ሰው የአፉ ጠረን የቂያም ቀን ከምስክ (ሽቶ) ሽታ የተሻለ ይሆናል :ለፆመኛ ሁለት ደስታዎች አሉት ደስታዎችም ፆመኛ ማታ ሲያፈጥርና በአኺራ ጌታውን ሲገናኝ ነው »ብለዋል ቡኻሪ ሙስሊምና ሌሎችም እንደዘገቡት

**2ኛ - አቡሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ባወሩት ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም)** *«የረመዳንን ፆም ግዴታ መሆኑን አውቆ (በኢማን) ምንዳም አገኝበታለሁ ብሎ (በኢሕቲሳብ) የፆመ ሰው ያለፈው ወንጀሉ ሁሉ ይማርለታል»* ብለዋል

ቡኻሪ ሙስሊምና ሌሎችም እንደዘገቡት

**3ኛ - ሱሄል ቢን ሰዕድ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ባወሩት ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም)** « ጀነት ውስጥ ረያን የሚባል በር አለ የቂያም ቀን ፂሚዎች ብቻ የታሉ ፂሚዎች ተብለው ከገቡበት በኋላ በሩ ይዘጋል ከነሱ በስተቀር ማንም አይገባበትም »**ብለዋል::** ቡኻሪ ሙስሊምና ሌሎችም እንደዘገቡት

ባጠቃላይ ፆም ማለት ሙእሚኖች ፀባያቸውን የሚያንፁበትና የሚያስተካክሉበት ትልቅ ትምህርት ቤት ነው ። ይኸውም ከነፍሰ ጋር የሚታገሉበት ፣ ስሜትን ከሸይጣን ጉትጎታ የሚከላከሉበት ፣ሰው የሚጎዳበትን ሃይለኝነቱን ዋጥ አድርጎ ትዕግስት ወደ ተላበሰ ሕይወት የሚመለስበት፣ሥርዐትና ደንብ የሚማርበት ፣ በልቡ ውስጥ እዝነትና ሩህሩህነት የሚፀድቅበት፣ ሙስሊሞች እርስ በርስ በመተዛዘን የሚተሳሰሩበትና የሚረዳዱበት ፣ ትልቅ ማዕከል ነው ።

## የፆም አይነቶች ሁለት ናቸው

*1ኛ - ግዴታ (ዋጂብ) የሆነ ፆምና*

*2ኛ - በውዴታ (ተጠውዕ) የሚፆም እንደ ሸዋል ፣ አሹራ ፣ ሰኞ ሃሙስ ፣ ዐረፋ ፣በየወሩ ሦስት ቀን : የመሳሰሉት ናቸው ።*

ግዴታ (ዋጂብ) የሆነው ፆም በሦስት ይከፈላል

*ሀ - ወቅቱን ጠብቆ የሚመጣው ግዴታ የሆነው የረመዳን ወር ፆም*

*ለ - ለጥፋት ማካካሻ የሚፆም (ከፋራ)*

*ሐ - ሰው በራሱ ላይ የሚጭነው የስለት ፆም (ነዝር) ናቸው።*

# የረመዳን ፆም ሕግ (ሑክም)

የረመዳን ፆም ግዴታ የሚሆንባቸው ለአካለ መጠን የደረሱ፣ የአዕምሮም ሆነ የአካል ጤነኞች ፡ ሙስሊም የሆኑና መንገደኛ ያልሆኑ ናቸው ::

የረመዳን ፆም ከአምስቱ የኢስላም መሠረቶች አንዱ ሲሆን ይኸውም በቁርአን በሐዲስና በሕዝበ ሙስሊሙ የተረጋገጠ ነው ::

ስለረመዳን ከቁርአን :-

قال تعالى: ﴿ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ كُتِبَ عَلَيْكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ ﴿١٨٣﴾ أَيَّامًا مَّعْدُودَٰتٍ ۚ فَمَن كَانَ مِنكُم مَّرِيضًا أَوْ عَلَىٰ سَفَرٍ فَعِدَّةٌ مِّنْ أَيَّامٍ أُخَرَ ۚ ..... ﴿١٨٤﴾ ﴾

(البقرة 183-184)

**ትርጉሙ (( እናንተ ያመናችሁ ሆይ ፆም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩ (ህዝቦች) ላይ እንደተደነገገ በናንተም ላይ ተደነገገ ልትጠነቀቁ ይከጀላል እና የተወሰኑ ቀኖች ( ፁሙ) ከናንተ ውስጥ በሽተኛ ወይንም በጉዞ ላይ የሆነ ሰው ከሌሎች ቀኖች የተወሰነውን መፆም አለበት .... ))** በቀራ // 183-184 //

ኢብኒ ዑመር (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ባወሩት ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ኢስላም በአምስት ነው የተገነባው ይኸውም :-

1ኛ - በሐቅ የሚገዙት ከአላህ በስተቀረ አምላክ እንደሌለና የረሱልን .
(ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) መልዕክተኛነት መመስከር ::

2ኛ - ሰላትን መስገድ ::

3ኛ - ከንብረት ላይ ግዴታ የሆነውን ዘካት ማውጣት ::

4ኛ - አቅሙ የቻለ በዕድሜው አንዴ ሐጅ ማድረግ

5ኛ - የረመዳንን ወር መፆም ናቸው::

አቡሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ባወሩት ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «የረመዳን ወር ሲገባ የሰማይ በሮች ይከፈታሉ የጀሃነም በሮች ይዘጋሉ ሸይጣኖችም ይታሰራሉ» ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት

# የረመዳን ወር መግባቱ እንዴት ይታወቃል

የረመዳን ወር መግባቱ በሁለት አይነት መንገድ ማወቅ ይቻላል:-

**1ኛ - የረመዳንን ወር ጨረቃ በማየት :- ለዚሁም አላህ በቁርአኑ**

قال تعالى: ﴿ ... فَمَن شَهِدَ مِنكُمُ ٱلشَّهۡرَ فَلۡيَصُمۡهُ .... ﴿١٨٥﴾ ﴾

ትርጉሙም **((... ከናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይፁመው ... ))** በቀራ 185

-- ወር ማግኘት ማለት በጨረቃ አቆጣጠር የጨረቃ ንዑስ ክፍል ምሽት ላይ ብቅ ብላ ስትታይ የወሩ መጀመርያ ሌሊት መግባቱ ይታወቃል :

ኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ባወሩት ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ወር ማለት ሃያ ዘጠኝ ሌሊቶች ናቸው (ጨረቃን) ሳታዩ አትፁሙ (ደመናና ጉም የመሳሰሉት) ከጋረዳቹሀ ግን ሰላሳውን (ሌሊቶች) ሙሉ»ብለዋል:: የቡኻሪ ዘገባ

ጨረቃ መውጣቷ የሚታወቀው በማየት ነው እንጂ በሒሳብ አይደለም በኢስላም ረመዳን ሲያዝም ሆነ ሲፈታ ሐጅም ሆነ ማንኛውም አቆጣጠር ጨረቃን በማየት ነው ወሩ መግባቱ የሚወሰነው ይህ ደግሞ ለዘመናት ሙሰሊሞቸ የተስማሙበት ነው ::

መጅሙዓ ፈታዋ ላይ ይመልከቱ

**2ኛ - የሻዕባንን ወር ሰላሳ ቀን መሙላት ሲሆን :-** እንደሚታወቀው የጨረቃ ወሮች አቆጣጠር ከሃያ ዘጠኝ ቀን አያንሱም ከሰላሳ ቀንም አይጨምሩም ስለዚህ በደመናም ሆነ በጉም ምክንያት የረመዳንን ወር ጨረቃ ማየት ካልተቻለ ሻዕባንን ሰላሳ ቀን መሙላት ብቸኛው አማራጭ ነው ይህ ሻዕባን ሰላሳኛው ቀን የጥርጣሬ ቀን (የውመ ሸክ ) ይባላል በዚህ ቀን ያስለመዱት ፆም ሲቀር ግዴታም ሆነ ትርፍ የሆነ ፆም መፆም ክልክል ነው

አቡሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ባወሩት ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ከናንተ ውስጥ ማንም ቢሆን ከረመዳን አስቀድሞ አንድም ቀን ቢሆን ወይንም ሁለት ቀን እንዳይፆም ነገር ግን ያስለመደው ፆም ካለ መፆም ይችላል » ብለዋል::

ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት

በተረፈ የጥርጣሬውን ቀን እንዳያልፈኝ ብሎ መፆም ትልቅ ጥፋት ነው -- ዓማር ቢን ያሲር (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳሉት (የጥርጣሬውን ቀን (የውመል ሸክ) የፆመ በእርግጥ አበልቃሲምን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ተቃወመ ማለት ነው አለ )

አቡ ዳውድ ተርምዚና ነሳኢ ዘግበውታል

(አበልቃሲም ማለት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የቃሲም አባት እየተባሉ የሚጠሩበት የቅፅል ስማቸው ነው)

# የረመዳን ጨረቃ (ሂላል)

# በአንድ ታማኝ ሰው እይታ ብቻ ስለመፅደቁ

የረመዳን ወር መግቢያ ጨረቃ (ሂላል) አንድ ሰው ብቻውን ካየ በሸሪዓው ምስክርነቱ ተቀባይነት አለው በዚህ አቋም አብዛኛዎቹ ዐሊሞች ይስማሙበታል :: ከነሱም አቢሐኒፋ ሻፊዒይና አሕመድ ሲሆኑ ኢብኑ ሙንዚርም ይህንኑ አቋም ይደግፉታል :: በተጨማሪ ኢማም ማሊክ፣ ለይስ፣ አል አውዘዒ፣ ሰውሪ፣ ሻፊዒይም ለጨረቃ እይታ አንድ ሰው በቂ ቢሆንም ታማኝ መሆን አለበት የሚለውን ሸርጥ ያስቀምጡታል:: የአንድ ሰው ለጨረቃ እይታ ምስክርነት በቂ ስለመሆኑ የኢብኑ ዑመር ሐዲስ ማስረጃ ነው ኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት (ሰዎች ሂላልን ሲፈልጉ እኔ አየኋት ሄጄም ለረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንደነገርኳቸው ፆምን ይዘው ሌሎችም እንዲፆሙ አዘዙ )አሉ::

አቡዳውድ ዳሪሚይ እና ኢብኑ ሒባን እንደዘገቡት::

የጨረቃን እይታ የአንድ ታማኝ ሰው ምስክርነት ፆሙ ሲያዝ ነው እንጂ የረመዳን ፆም ሲፈታ መስካሪዎች ሁለት መሆን አለባቸው የሚል ማስረጃ አለ::
የጨረቃን እይታ ምስክርነት ወንድም ሆነ ሴት ብትሆን ለውጥ የለውም:

# ለትክክለኛ ፆም መሟላት ያለበት (ሹሩጥ)

*1ኛ - ኒያ ማድረግ :- ኒያ ማለት አንድን ነገር ለመሥራት ፍፁም ሆኖ መወሰንና ከልብ ጋር መስማማት ማለት ነው :: የረመዳን ፆም ከኢስላም ዒባዳዎች አንዱ በመሆኑ ያለ ኒያ መፆም ተቀባይነት የለውም ::*

አላህም በቁርአኑ :-

﴿ وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا لِيَعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مُخۡلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ حُنَفَآءَ وَيُقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤۡتُواْ ٱلزَّكَوٰةَۚ وَذَٰلِكَ دِينُ ٱلۡقَيِّمَةِ ٥ ﴾

ትርጉሙም **((ለአላህ ሃይማኖትን ለርሱ ብቻ አጥሪዎች ቀጥተኞች ሆነው ሊገዙት ሰላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ ዘካንም ሊሰጡ እንጂ ያልታዘዙ ሲሆኑ (ተለያዩ):: ይህ የቀጥተኛይቱ (ሃይማኖት) ድንጋጌ ነው::))** አል በይናህ -5

ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «*ሥራዎች ሁሉ በኒያ ነው* ብለዋል»

*ፆምን ያለ ኒያ ከሰው ጋር ለመመሳሰል ብሎ ወይንም እንደባሕል ቆጥሮ ወይንም ለሰውነት ማስተካከያ ለስፖርት ብሎ መፆም በአላህ ዘንድ ምንም ምንዳን አያስገኝም :: ኢማሙ ነወዊ (ረሒመሁሏህ) ፆም ያለኒያ አይሆንም የኒያ ቦታው ደግሞ ልብ ነው ብለዋል ::*

ኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ከሙእሚኖች እናት ሐፍሳ (ረዲየሏሁ ዓንሃ) ሰምተው እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ከፈጅር በፊት ፆምን ያልያዘ ፆም የለውም» ብለዋል መያዝ ማለት የሚያመለክተው ኒያን ነው ::

በተጨማሪ የግዴታ (ፈርድ) ፆም ሲሆን ነው ከፈጅር በፊት ኒያ ግዴታ የሚሆነው ነገር ግን ግዴታ ያልሆነ ትርፍ (ነፍል) ፆም በቀንም ቢሆን ኒያ ማድረግ ይቻላል ::

**2ኛ - ሴት ከወርአበባና ከወሊድ ደም የጠራች መሆን አለባት ::**

## በረመዳን ለእያንዳንዱ ቀን ይነየታል?
## ወይንስ ለሙሉ ወር አንዴ ከነየቱ በቂ ነው ?

-- በረመዳን ፆም ለያንዳንዱ ቀን ሌሊት ላይ ፅኑ የሆነ ኒያ መነየት ያስፈልጋል ::

እዚህ ላይ የዓሊሞች ልዩነት አለ አብዛኛዎቹ ዐሊሞች የሐፍሳ (ረዲየሏሁ ዓንሃ) ሐዲስ በመንተራስ ለያንዳንዱ ቀን ሌሊት ኒያ ያስፈልገዋል ይላሉ ምክንያቱም አንድ ቀን እራሱን የቻለ ዒባዳ ነው ከሌላው ቀን ጋር ምንም ግንኙነት የለውም እንዲያውም ወሩን ሁሉ የነየተ ሰው በመሃል በምክንያት ቢያቋርጥ የቀጠላቸው ቀኖች ያለኒያ ፆመ ማለት ነው ስለዚህ ለያንዳንዱ ቀን ሌሊቱን መነየት ያስፈልጋል ::

ሌሎች ዐሊሞች ደግሞ እነ ዘፍር፡ ማሊክና፡ አሕመድ፡ እንደሚሉት የወሩ መጀመርያ ላይ ለወር መነየት ይቻላል ለምሳሌ እንደ ሐጅ ሥራ፣ ተከታታይ የሆኑት ማካካሻ (ከፋራ) ፆም የመሳሰሉት በአንዴ ነይቶ ብዙ ስለሚሰራባቸው ለረመዳንም ፆም አንዴ ከነየቱ ይበቃል ይላሉ ::

# የፆም መዐዘን (ሩክን)

ፆም ሲባል ትርጉሙ ከፈጅር ጀምሮ ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ፆምን ከሚያበላሹ (ከሚያስፈጥሩ) ነገሮች መቆጠብ ወይንም መታቀብ (ኢምሳክ) ማለት ነው አላህም በቁርአኑ ሲያብራራ:-

قال تعالى: ﴿ أُحِلَّ لَكُمْ لَيْلَةَ ٱلصِّيَامِ ٱلرَّفَثُ إِلَىٰ نِسَآئِكُمْ ۚ هُنَّ لِبَاسٌ لَّكُمْ وَأَنتُمْ لِبَاسٌ لَّهُنَّ ۗ عَلِمَ ٱللَّهُ أَنَّكُمْ كُنتُمْ تَخْتَانُونَ أَنفُسَكُمْ فَتَابَ عَلَيْكُمْ وَعَفَا عَنكُمْ ۖ فَٱلْـَٔـٰنَ بَـٰشِرُوهُنَّ وَٱبْتَغُوا۟ مَا كَتَبَ ٱللَّهُ لَكُمْ ۚ وَكُلُوا۟ وَٱشْرَبُوا۟ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَكُمُ ٱلْخَيْطُ ٱلْأَبْيَضُ مِنَ ٱلْخَيْطِ ٱلْأَسْوَدِ مِنَ ٱلْفَجْرِ ۖ ثُمَّ أَتِمُّوا۟ ٱلصِّيَامَ إِلَى ٱلَّيْلِ ۚ وَلَا تُبَـٰشِرُوهُنَّ وَأَنتُمْ عَـٰكِفُونَ فِى ٱلْمَسَـٰجِدِ ۗ تِلْكَ حُدُودُ ٱللَّهِ فَلَا تَقْرَبُوهَا ۗ كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ ٱللَّهُ ءَايَـٰتِهِۦ لِلنَّاسِ لَعَلَّهُمْ يَتَّقُونَ ١٨٧ ﴾

**ትርጉም ((በፆም ሌሊት ወደ ሴቶቻችሁ መድረስ ለናንተ ተፈቀደላችሁ እነርሱ ለናንተ ልብሶች ናቸው እናንተም ለነርሱ ልብሶች ናችሁ አላህ እናንተ ነፍሶቻችሁን ምትበድሉ መሆናችሁን ዐወቀ በናንተም ላይ ተመለሰላችሁ (ፀፀታችሁን ተቀበለ) ለናንተም ይቅርታ አደረገ አሁን ተገናኙዋቸው አላህም ለናንተ የፃፈላችሁን ነገር (ልጅን) ፈልጉ ከጎህ የኾነው ነጩ ክርም ከጥቁሩ ክር (ከሌሊት ጨለማ) ለናንተ እስከሚገልፅላችሁ ድረስ ብሉ ጠጡም ከዚያም ፆምን እስከ ሌሊቱ ድረስ ሙሉ እናንተም በመስጊዶች ተቀማጮች ስትኾኑ አትገናኙዋቸው ይህች የአላህ ሕግጋት ናትና (ለመተላለፍም) አትቅረቧት እንደዚሁም አላህ አንቀፆችን ለሰዎች ያብራራል እነሱም (ሰዎች የተከለከሉትን) ሊጠነቀቁ ይከጀላልና))** አል በቀራህ - 187

*ይህ አንቀፅ አላህ በፆም ሌሊት ፆምን የሚያገድፉ (የሚያስፈጥሩ) ነገሮች ሁሉንም ግብረ-ሥጋ ግንኙነትን ጨምሮ መፈቀዱን ያመለክታል* በተጨማሪ ነጩ ክር ከጥቁሩ ክር እስኪገለፅላችሁ ማለቱ ፈጅር እስኪደርስ ማለቱ ነው ::

# የፆም ሱናው እና ሥርዓቱ (አደቡ)

## ሱሑር

- ስለ ሱሑር አነስ ኢብኑ ማሊክ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ሱሑር አድርጉ በሱሑር ውስጥ በረካ አለ» ብለዋል

ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት

-- ዓምር ቢን አል ዐስ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «በእኛ ፆምና በአህለል ኪታቦች ፆም መካከል ያለው ልዩነት ሱሑር መብላት ነው» ብለዋል::

አቡዳውድና ተርምዚ እንደዘገቡት

-- ዓብደላህ ኢብኑ ዓምር (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ሱሑር አድርጉ በአንድ ጉንጭ ውሃም ቢሆን » ብለዋል

-- አቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ከሙእሚን ሱሑር የተሻለው ተምር ነው» ብለዋል፡፡ አቡዳውድና ኢብኑ ሒባን እንደዘገቡት

## ሱሑርን ስለማዘግየት

- አነስ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ዘይድ ኢብኑ ሳቢት (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዲህ አለ አሉ (ከረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ጋር ሱሑር ከአደረግን በኋላ (ትንሽ ቆይተው) ወደ ሰላት ቆሙ አለ ምን ያህል ጊዜ ይሆናል? ስለው ሃምሳ የቁርአን አንቀፅ የሚቀራበት ጊዜ ይሆናል አለኝ፡፡

-- አኒሳ ቢንት ሐቢብ (ረዲየሏሁ ዓንሃ) እንዳወራችው / ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ኢብኑ ኡሙ መክቱም የመጀመርያውን አዛን ሲያዝን ብሉ ጠጡም የሁለተኛውን አዛን ቢላል ሲያዝን እንዳትበሉ እንዳትጠጡም» አሉን ከመካከላችን አንዷ ከሱሑሯ ጥቂት ከቀራት ለቢላል ሱሑሬን እስካጠናቅቅ ረጋ በል ትለው ነበር / ሰነዱ ትክክለኛ ሲሆን በዚህ መልኩ ያቀረበው ነሳኢ ነው አሕመድና ኢብኑ ሒባንም ዘግበውታል

## በኢፍጣር ስለመቻኮል

-- ሱሄል ቢን ሰዕድ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ሰዎች በፉጡር እስከተቻኮሉ ድረስ ከመልካም (ሕይወት) አይርቁም » ብለዋል፡፡

-- ዓብደላህ ኢብኑ አቢ ዓውፊ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ከረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ጋር በጉዞ ላይ እያለን ፆመኛ ነበሩ ፀሓይ እንደጠለቀች ከሰዎች መካከል ለአንዱ (ማፍጠሪያ) አዘጋጅልን አሉት ሰውዬውም ጥቂት ቢያመሹ ? አላቸው እሳቸውም ሦስት ጊዜ ደጋግመው ሂድ አዘጋጅልን ... አሉት ሄዶም አዘጋጀላቸው ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ከጠጡ በኋላ «ምሽት በዚህ በኩል ብቅ ሲል ካያቹህ ፆመኛ አፈጠረ ማለት ነው» አሉ፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት

ከዚህ ሐዲስ የምንረዳው ፆመኛ የሚያፈጥረው ጀንበር እንደጠለቀች ነው እንጂ አንዳንድ ቦታ እንደሚታየው የግድ ጨለማ እስኪሆን መጠበቅ ስህተት ነው ::

--- አነስ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሲያፈጥሩ (ከመኽሪብ) ሰላት በፊት ካገኙ እሸት በሆነ ተምር ካላገኙም በበሳል ተምር ከጠፋም በውሃም ቢሆን ያፈጥሩ ነበር::

-- ለፆመኛ በጣፋጭ ነገር ማፍጠር የተመረጠ ነው ሃይል ይጨምርለታል ጣፋጭ ነገር ካልተገኘ ውሃም ቢሆን በጣም ጠቃሚ ነው በተለይ ከምግብ በፊት ፆመኛ ትንሽ ውሃ ሲቀምስ በፆም የደረቀ ጉበቱን ያረጥብለታል የፆመኛ ሰው ጉበት ድርቀት ስለሚሰማው መጀመርያ በውሃ ከረጠበ በቀጣዩ የምግብ ሂደት በደንብ ሊጠቀም ይችላል::

ተምርና ውሃ ለልብ በጣም ትልቅ ጥቅም አላቸው ጥቅሙንም የልብ ሐኪሞች ጠንቅቀው ያቁታል :: ከኢብኑ ቀይም ዛደል መዓድ ላይ ይመልከቱ

## በፊጥር ወቅት የሚደረግ ዱዓ

ኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳሉት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሲያፈጥሩ «ዘሃበ ደመኡ ወብተለተል ዑሩቅ ወሰበተል አጅር ኢንሻ አላህ »ይሉ ነበር ትርጉሙም «ጥም ተወገደ የደም ሥርም ረጠበ የአላህ ፍቃዱ ከሆነ ምንዳውም ፀደቀ » ማለት ነው:: አቡ ዳውድና ነሳኢ ዘግበውታል

## ቁርአን መቅራት በረመዳን

በረመዳን ቁርአን መቅራት ማብዛት በጣም የተወደደ ነው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በረመዳን ከጅብሪል ጋር ሲገናኙ ከምንግዜውም በበለጠ ይተጉ ነበር

# ፆም የሚያበላሹ ወይንም ምንዳ የሚቀንሱ ነገሮች

-- ፆም ግልፅ በሆነ በመብላት በመጠጣትና በግንኙነት ብቻ ሳይሆን ግልፅ ባልሆኑ ነገሮች ምንዳው ሊቀንስ ይችላል ይኸውም አፀያፊ ቃል በመናገር፣ በሃሜት፣ በማሳበቅ፣ በጭቅጭቅና በመጣላት ምክንያት ፆም ምንዳው ይቀንሳል አላህም ፆምን የደነገገበት ዋና ምክንያት ሙእሚን በኢስላማዊ ሥነ- ምግባር ታንፆ አላህን እንዲፈራውና እንዲጠነቀቅ ነው ከቁርአንም አንቀፅ :-

قال تعالى: ﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ...... ﴿١٨٣﴾ ﴾

**ትርጉሙም (( እናንት ያመናችሁ ሆይ ፆም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩ (ህዝቦች) ላይ እንደተደነገገ በናንተም ላይ ተደነገገ ልትጠነቀቁ ይከጀላል እና ))**
**አል በቀራህ 183-**

ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ) ወሰለም «(አንድ ፂሚ) ፀያፍ ንግግሮችንና ፀያፍ ተግባሮችን ካልተወ በስተቀር ምግብና መጠጥ በመተው ለአላህ ጉዳዩ አይደለም» **ብለዋል::** ቡኻሪ አቡ ዳውድና ተርምዚ ዘግበውታል

ሃሜትና ፀያፍ ቃል በቀጥታ ፆምን ያበላሻል ወይንስ አያበላሽም በሚለው ነጥብ የዐሊሞች ልዩነት ቢኖርም ለማንኛውም ከሃሜትና ከፀያፍ ቃል መራቁ ሰላማዊ ጉዞ ነው ::

## በግልፅ ፆም የሚያበላሹ (የሚያስፈጥሩ) ነገሮች

1ኛ - እያወቁ ሳይረሱ መብላትና መጠጣት

2ኛ - ግብረ-ሥጋ ግንኙነት መፈፀም

3ኛ - አውቆ ማስታወክ

4ኛ - ሴቶች የወር አበባና የወሊድ ደም በቀን ከመጣባቸው

5ኛ - የዘር ፈሳሽ አውቆ ማስወጣት

6ኛ - አፈጥራለሁ ብሎ በልብ መወሰን (መነየት)

7ኛ - ከኢስላም መውጣት (መክፈር)
8ኛ - ዋግምት ማድረግ ፡ ናቸው

## የፆም መበላሸት በሁለት ይከፈላል

1ኛ - ፆም መሆኑን እያወቀ በተለያዩ ምክንያቶች የበላና የጠጣ ያፈጠረበትን ቀን ልክ መተካት (ቀዷ) ማውጣት ግዴታ ነው ፡፡

- በፆም ወቅት በመርሳት የበላና የጠጣ ፆሙ ስለማይበላሽ እንዳስታወሰ መብላቱንና መጠጣቱን አቋርጦ ፆሙን መቀጠል ይችላል ከሐዲስ መረጃ

--አቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ፆመኛ ሆኖ እረስቶ የበላ ወይንም የጠጣ ፆሙን ይጨርስ ምክንያቱም አላህ ነው ያበላውና ያጠጣው » ብለዋል፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል ፡

ፆሙ ፈርድም ቢሆን ነፍል ለውጥ የለውም፡፡

2ኛ - የመሽ ወይንም ገና ያልነጋ መስሎት የበላና የጠጣ ወይንም የተገናኘ ፆሙን መቀጠል አለበት ወይንስ መካስ (ቀዷ) አለበት ? በዚህ ላይ የዐሊሞች ልዩነት ቢኖርም

- የመሽ ወይንም ገና ያልነጋ መስሎት ፆሙን ያበላሸ መካስ (ቀዷ) ማውጣት አለበት ይህ የአራቱም አኢማዎች አቋም ነው ፡፡

## ፆሙ ተበላሽቶ ከፋራ የሚያስገድድ

--አቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ዘንድ ተሰባስበን ቁጭ እንዳልን አንድ ሰው መጥቶ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ጠፋሁኝ አላቸው «ምን ሆንክ» አሉት ፆመኛ ሆኜ ሚስቴ ላይ ወደቅኩኝ (ተገናኘኋት) አላቸው ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ባርያን ነፃ ማውጣት ትችላለህ» አሉት አልችልም

አላቸው «ሁለት ወሮችን በተከታታይ መፆም ትችላለህ አሉት » አልችልም አላቸው «ስልሳ ምስኪን ማብላት ትችላለህ አሉት»አልችልም አላቸው ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ጥቂት ዝም ካሉ በኋላ እዛው ባለንበት በዕቃ ተምር አምጥተው «ይህንን ውሰድና ተሰደቅበት» አሉት ሰውዬውም ተምሩን ተቀብሎ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ በከተማው ከዳር እስከዳር ከኔ የባሰ ድሐ የለም አላቸው ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ፈገግ ብለው እየሳቁ «በል ቤተሰብህን» አብላ አሉት::

ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል

-- ሌላው ሚስቱን በረመዳን ፆም አውቆ የተገናኘ ማካካሻው በወንዱ ላይ ብቻ ሳይሆን በሚስትየውም ከተስማማችና ወዳ ከገባችበት ከፋራ አለባት ነገር ግን ሚስት ያለፍላጎቷ የተገደደች ከሆነ ከፋራ የለባትም ::

-- በረመዳን ፆም በቀን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ የከፋራው ቅደም ተከትል መጀመርያ ባርያ ነፃ ማውጣት ካልቻለ ሁለት ወር አከታትሎ መፆም ካልቻለ ስልሳ ምስኪን ማብላት ነው

--- በረመዳን ፆም በቀን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ ከፋራውን ቢያወጣም ባያወጣም በድጋሚ በሌላ ቀን ለሁለተኛ ጊዜ ግንኙነት ከፈፀመ የሁለት ቀን ከፋራ ማውጣት ግዴታው ነው ነገር ግን በአንድ ቀን ውስጥ ደጋግሞ የተገናኘ ከፋራው አንዴ ብቻ ነው ::

# የፆመኛ ትጥበት በቀን

ፆመኛ የሆነ ሰው በቀን በከፊልም ሆነ በሙሉ አካላቱን ቢታጠብ ፆሙ አይበላሽም ::

--ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በረመዳን ከፈጅር በፊት ከግንኙነት በኋላ ገላቸውን ሳይታጠቡ (ጁኑብ) ሆነው ከፈጅር በኋላ ገላቸውን ታጥበው ፆመዋል ::

-- ከሰሐባዎች አንዱ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ፆመኛ ሆነው ጥም ወይንም ሙቀት ለማስወገድ በራሳቸው ላይ ውሃ ያፈሱ ነበር ብሎ አውርቶዋል ::

አቡዳውድ ዘግበውት ሼኽ አልባኒ ትክክል ብለውታል

# ፆመኛ መጉመጥመጥና በአፍንጫው ውሃን ስለመሳብ

ፆመኛ የሆነ ሰው በቀን አፉን እንደፈለገ መጉመጥመጥ ሲችል በውዱ ወቅት በአፍንጫው ውሃ ሲስብ ግን ወደ ውስጥ መሳብ የለበትም::

-- ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ፆመኛ ካልሆናቹህ (በውዱዕ ጊዜ) ውሃን በአፍንጫ ወደ ውስጥ አድርሱ» ብለዋል ስለዚህ ፆመኛ የሆነ ሰው በውዱ ጊዜ በአፍንጫው ውሃ በጣም መሳብ የለበትም::

-- ፆመኛ በውሃ ሲጉመጥመጥ ምናልባት ትንሽ ውሃ ወደ ጉሮሮው ቢደርስና ቢያመልጠው መመለስ እስካልቻለ ድረስ ፆሙ አይፈርስበትም ::

# ፆመኛ ምግብ ስለመቅመስ

-- ኢብኑ ዓባስ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ፆመኛ የሆነ ሰው ወደ ጉሮሮው እስካልገባ ድረስ ፈሳሽ ሆነ ሌላ ነገር ቢቀምስ ምንም አይደለም ብለዋል::

-- ሼኽል ኢስላም ኢብኑ ተሚየህ ፆመኛ ያለምክንያት ምግብ መቅመሱ የተጠላ ሲሆን ፆምን ግን አያፈርስም በምክንያት የቀመሰ ሰው በውሃ ከመጉመጥመጥ አይለይም ብለዋል :: መጅሙዓ ፈታዋ 25/266

# ዋግምት ወይንም ደም መለገስ ለፆመኛ

ዋግምት ማለት ከሰውነት ውስጥ ቆሻሻ ደም በምላጭ እየተበጣ ወይንም በቀንድ እየተመጠጠ የሚያስወግዱበት ባሕላዊ የሕክምና ዘዴ ነው

-- ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ዋግምት ያደረገም የተደረገለትም አፈጠሩ ) ብለዋል::

# ፆመኛ በቀን ጥርሱን ስለመፋቅ

-- ለፆመኛ በቀን ጥርሱን መፋቅ የሚከለክለው ምንም ሐዲስ የለም በፈለገው ጊዜ መፋቅ ይችላል በዚህ የሐዲስ ተንታኞች (ፋቀሃዎች) ሁሉም ይስማሙብታል ነገር ግን አብዛኛዎቹ ሻፊዒዮችና ሐንበልዮች ጥርስን ከዙሁር በኋላ መፋቁ ይጠላል ምክንያቱም ከአፉ የሚወጣው የፆመኛ ሰው የአፍ ጠረን ከተፋቀ መጥፎ ጠረን አይኖረውም የጠረኑ መኖር አላህ ዘንድ ከምስክ ሽቶ የበለጠ ያማረ ሽታ አለውና ቢሉም ፆመኛ ዋና የአፉ ጠረን የሚወጣው ከሆዱ ስለሆነ በፈለገው ጊዜ መፋቁ ችግር አያመጣም ::

-- የጥርስ ማፅጃ ኮልጌት የመሳሰሉትን ፆመኛ በቀን መጠቀሙ የሚከለክለው ነገር የለም ነገር ግን ወደ ጉሮሮው እንዳይገባ መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው ኮልጌቱን በማታ መጠቀሙ ደግሞ የተመረጠ ነው ::

# ፆመኛ አክታን ስለመዋጥ

--- ከአፍንጫ ወይንም ከደረት አካባቢ በድንገት የሚመጣ አክታን ወደ አፍ ሳይደርስ መዋጥ ፆምን አያበላሽም ምክንያቱም መቆጣጠር አይቻልምና ነገር ግን አክታ ወደ አፍ ከደረሰ በኋላ እያወቁ መዋጥ ፆምን ያበላሻል ::

# በሕመም ምክንያት የሚያፈጥሩ

## በሕመም ምክንያት የሚያፈጥሩ በሦስት ይከፈላሉ

1ኛ - ሕመምተኛ የሆነ ፂሚ ታግሶ ቢፆም የተጠላ ነው ቢያፈጥርም ችግር የለበትም::

2ኛ - የከባድ በሽታ ሕመምተኛ ሆኖ ለሕይወቱ የሚያሰጋው ከሆነ ማፍጠር ግዴታው ነው አላህ በቁርአኑ :-

قال تعالى: ﴿ شَهۡرُ رَمَضَانَ ٱلَّذِيٓ أُنزِلَ فِيهِ ٱلۡقُرۡءَانُ هُدٗى لِّلنَّاسِ وَبَيِّنَٰتٖ مِّنَ ٱلۡهُدَىٰ وَٱلۡفُرۡقَانِۚ فَمَن شَهِدَ مِنكُمُ ٱلشَّهۡرَ فَلۡيَصُمۡهُۖ وَمَن كَانَ مَرِيضًا أَوۡ عَلَىٰ سَفَرٖ فَعِدَّةٞ مِّنۡ أَيَّامٍ أُخَرَۗ يُرِيدُ ٱللَّهُ بِكُمُ ٱلۡيُسۡرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ ٱلۡعُسۡرَ.... ﴾

**ትርጉም ((....ቁርአን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው ከናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይፁመው ሕመምተኛ ወይንም በጉዞ ላይ የኾነም ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን (በልኩ) መፆም አለበት አላህ በናንተ ገሩን ነገር ይሻል በናንተም ችግሩን አይሻም ....))**

**አል በቀራህ 185**

**--- መንገደኛ በጉዞው ወቅት መፆሙ ምንም ችግር የማይፈጥርበት ከሆነ መፆም ይችላል ነገር ግን ጉዞው በፆሙ ምክንያት በጤናው ላይ ችግር የሚያመጣ ከሆነ ማፍጠሩ ግዴታ ነው ::**

**3ኛ - ያለበቂ ምክንያት በቀላል ሕመም ለማፍጠር መቸኮሉ ተገቢ አይደለም ቀላል ራስምታት ሆድ ቁርጠት የጥርስ ህመም የመሳሰሉት አያስፈጥሩም ::**

## የሽማግሌዎች የአረጋዊያንና የከባድ ሕመምተኞች ፆም

**--- እድሜያቸው በጣም የገፋ ሽማግሌዎችና አረጋዊያን ወይንም የመዳን ተስፋ የሌላቸው ሕመምተኞች በረመዳን ፆም ማፍጠር ይፈቀድላቸዋል በምትኩ በየቀኑ ለምስኪን ማብላት አለባቸው::**

## የእርጉዝ ሴት ፆም

**-- በእርግዝና ላይ ያለች ሴት መፆም ካልቻለች ማፍጠር ትችላለች ያፈጠረችባቸውን ቀኖች ቀዷ ስታወጣ ለምስኪን የማብላት ግዴታ ግን የለባትም ::**

በወር አበባና በወሊድ ደም ላይ ያሉ ሴቶች መፆማቸው ሐራም ነው ፍፁም ሳይጠሩ ፆም ግዴታ አይሆንባቸውም በጠሩ ግዜ ግን ሌላ ረመዳን ሳይደረብ እንደተመቻቸው ቀዷ ያወጣሉ:: ሙግኒና መጅሙዓ ይመልከቱ

--- ሴት እኩለ ቀን ላይ ከወር አበባ ከጠራች ግማሹን ቀን መፆም የለባትም እንዳፈጠረች መቀጠል አለባት መብላት መጠጣትም ሆነ አጋጣሚ መንገደኛ ሆኖ ያፈጠረ ባሏን መገናኘት ትችላለች ::

--- ሴት ከፈጅር በፊት ከወር አበባ ከጠራች ኒያ አድርጋ መፆም ትችላለች ለመታጠቡ ከፈጅር አዛን በኋላ ቢሆንም ምንም ችግር አይፈጥርም::

## ሴቶች የወር አበባን የሚያቆም ኪኒን ስለመውሰድ

-- በመሠረቱ የወር አበባ በአደም ሴት ልጆች ላይ አላህ የፃፈው በመሆኑ በዚህ ወቅት ቢያፈጥሩ ብዙ ሊያስጨንቃቸው አይገባም ኪኒኑን መጠቀሙ የሚወደድ አይደለም ነገር ግን ኪኒኑ ጤንነታቸውን የማይነካ ከሆነና ደሙን ሙሉ ለሙሉ የሚያቆመው ከሆነ ኪኒኑን በመውሰድ መፆም ይችላሉ ::

## በሴቶች ላይ የማያቋርጥ ደም (ኢስቲሐዳ)

-- ሴቶች ላይ ከወር አበባ በተለየ መልኩ ቶሎ የማያቋርጥ ደም ሊመጣባቸው ይችላል ይህ ደም አይነቱ ከወር አበባ ደም ፍፁም የተለየ ነው በዚህን ግዜ ሰላትም ሆነ ፆም መተው ተገቢ አይደለም እየተጠነቀቁ መስገድና መፆምም ይችላሉ ::

## የረመዳን ቀዷ

በረመዳን ፆም ያለምክንያት ያፈጠረ ሰው ቀዷውን ፆሞ ከተውበትና ከፀፀት ጋር ከፋራም ማውጣት አለበት ይህ የአብዛኛው ዐዓሊሞች አቋም ነው ::

--- የረመዳን ቀዳ ያለበት በምክንያትም ሆነ ያለምክንያት በፈለገበት ጊዜ ቀዷ ማውጣት ይችላል ::

-- የሙእሚኖች እናት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዓንሀ) (በረመዳን ያመለጠኝን ፆም ካለ ስለማልችል እስከ ሻዕባን ድረስ አቆየው ነበር) ይላሉ

-- የረመዳን ቀዷ እያለበት ቀዷውን ሳያወጣ ሌላ ረመዳን የተደረበበት ሰው የተደረበውን ረመዳን ፆም ሲጨርስ ያለፈውን ረመዳን ቀዳ ያወጣል የተደረበበት በምክንያት ከሆነ ቀዳ ብቻ አውጥቶ ከፋራ መክፈል የለበትም::

ነገር ግን የመጀመርያውን ቀዳ ሳያወጣ ሌላ ረመዳን የተደረበበት ያለምክንያት ከሆነ ቀዳውን ሲያወጣ በያንዳንዱ ቀን ለምስኪ ማብላት አለበት ::

--- ቀዷ ያለበት ሰው ቀዷ ሲያወጣ የግድ በተከታታይ ይሁን አይባልም አቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ዊትር እያደረገ ያውጣ ሲሉ አነስ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ከፈለገ በተከታታይ ይፁም ካልፈለገ ሳያከታትል ቀዷ ማውጣት ይችላል ብለዋል::

--- የረመዳን ፆም ቀዷ ኖሮበት ሳይፆም የሞተ ቤተሰቡ ሊፆምለት ይችላል ::

-- ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ፆም እያለበት የሞተ ቤተሰቡ ይፁምለት » ብለዋል::

# የፍላጎት ፆሞች (ተጠውዕ)

## ከረመዳን ውጪ በፍላጎት የሚፆሙ ፆሞች

### የሸዋል ፆም

- የሸዋል ፆም:- ረመዳንን ወር ፆሞ በሸዋል ወር ስድስት ቀን የፆመ አመቱን ሙሉ እንደፆመ ነው :: ሰውባን (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) « የረመዳንን ወር የፆመ ወሩ እንደ አስር ወር ይታሰባል (ከዒድ) ፊጥር በኋላ ስድስት ቀን ሲጨመርበት አመት ሙሉ ሆነ ማለት ነው» ብለዋል ::
- 

አህመድ : ነሳኢና ኢብኑ ማጃህ : ዘግበውታል ::

## የዓሹራ ፆም

- በሙሐረም ወር ፆም በጣም የተወደደ ነው አቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ከረመዳን ቀጥሎ የተወደደ ፆም የአላህ ወር ሙሐረም ነው ከፈርድ ሰላት ቀጥሎ የተወደደው የሌሊት ሰላት ነው»ብለዋል

ሙስሊም ነሳኢና ኢብኑማጃህ ዘግበውታል

-- አቢ ቀታዳ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «የዓሹራ ቀን መፆም አላህ ዘንድ ያለፈውን አንድ አመት ያስምራል» ብለዋል፡፡

ሙስሊም ዘግበውታል

-- የዓሹራ ፆም የሚውለው ሙሐረም አሥረኛው ቀን ላይ ነው

## ሻዕባን ወር ላይ ፆም ማብዛት

-- ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዓንሃ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የሻዕባንን ወር አላፈጠሩም እስክንል ድረስ አዘውትረው ይፆሙ ነበር አንዳንዴ ደግሞ አልፆሙም እስክንል ድረስ አዘውትረው ያፈጥሩ ነበር ፡ - ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ከረመዳን በስተቀር ሙሉ ወር አይፆሙም እንደ ሻዕባን አዘውትረው የሚፆሙበት ወር የለም ነበር) ብለዋል፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል

--- የሻዕባን ወር ግማሽ ላይ (ኑስፍ ሻዕባን) እየተባለ የሚታወቅ ፆም የለም በአንዳንድ ሙስሊሞች ዘንድ ልዩ ጥቅም አለው የሚባለው ይህ ጾም ከረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የተገኘ አይደለም የፈጠራ ስራ (ቢድዓ) ነው ፡፡ ሻዕባን ግማሽ ሲሆን ሌሊቱን ቆማቹህ ቀኑን ፁሙ የሚባለው ኢብኑ ማጃህ ቢዘግቡትም በጣም ደካማ ሐዲስ ነው ፡፡

## የዓረፋ ቀን ፆም

--- ሐጅ ለማያደርጉ ሰዎች የዓረፋ ቀን ፆም በጣም የተወደደ ነው ።

አቢ ቀታዳ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «የዓረፋን ቀን መፆም አላህ ዘንድ ያለፈውን አንድ አመትና የመጪውን አመት ያስምራል » ብለዋል። ሙስሊም ዘግበውታል

## የሰኞ እና የሐሙስ ፆም

--- ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዓንሃ) እንዳወሩት (ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በሰኞና ሐሙስ ቀን ፆም ይተጉ ነበር) ብለዋል። ተርምዚ ነሳኢና ኢብኑ ማጃህ ዘግበውታ

--- ኡሳማ ቢን ዘይድ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ለረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሰለ ሰኞና ሐሙስ ቀኖች ፆማቸው ሲጠይቃቸው ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «እነዚህ ሁለት ቀኖች ሥራዎች ወደ አለማቱ ጌታ (አላህ) የሚቀርቡበት ቀኖች ናቸው እኔም ሥራዬ ፆመኛ ሆኜ እንዲቀርብ እፈልጋለሁ) አሉ።

ነሳኢ አህመድና በይሃቂ ዘግበውታል።

## በየወሩ ሦስት ቀን መፆም

--- አቢ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) (ወዳጄ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በሦስት ነገር አደራ አሉኝ ይኸውም ፡ በየወሩ ሦስት ቀን መፆም፣ የአዱሐ ሰላት፣ እና ከመተኛቴ በፊት ዊትር እንድሰግድ ) አሉ። ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል

--- ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ለዓብደላህ ቢን ዐምር (ረዲየሏሁ ዓንሁ) «በየወሩ ሦስት ቀን ፁም ሐሰናቱ በአሥር ሲባዛ አመት እንደተፆመ ነው) አሉት ።

ነሳኢ አቡ የዕላ እና ጠብራኒ ዘግበውታል

## ባለትዳር ሴት ስትፆም ባሏን ስለማስፈቀዷ

--- ባለትዳር ሴት የፍላጎት (ተጠውዕ) ፆም ስትፆም ባሏን ማስፈቀድ አለባት። አቢ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ሴት ባሏ አጠገቧ እያለ ያለፈቃዱ አትፁም » ብለዋል ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል

## አመቱን ሙሉ ስለመፆም

**--- አቢ ቀታዳ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ዑመር (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ለረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) አመቱን ሙሉ ለሚፆም እንዴት ነው ብለው ጠየቋቸው « ፆምም የለው ፌጥርም የለው » ብለው መለሱለት ::** ሙስሊም ዘግበውታል

## ስለ ረጀብ ፆም

**በረጀብ ላይ ልዩ የሆነ ፆም የለም ከረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ተገኘ የሚባለው ሐዲስ ሁሉ ደካማና ውሸት ነው ::**

**-- ዓጣእ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንደሚሉት ኢብኑ ዓባስ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) በዓል ሆኖ እንዳይቀር በመስጋት በረጀብ ወር ፆም ይከለክሉ ነበር ::**

## ለይለቱል ቀድር

**የመወሰኛይቱ ሌሊት (ለይለቱል ቀድር) በረመዳን ወር የምትመጣ አንድ ሌሊት ናት በዚህች ቀን ለአላህ በመታዘዝ ያሳለፈ ቡዙ ጥቅሞች ያገኛል ቀኗ የአንድ ሺ ወር ያህል ግምት አላት :አላህም በቁርዓኑ :-**

قال تعالى: ﴿ إِنَّآ أَنزَلۡنَٰهُ فِي لَيۡلَةِ ٱلۡقَدۡرِ ١ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا لَيۡلَةُ ٱلۡقَدۡرِ ٢ لَيۡلَةُ ٱلۡقَدۡرِ خَيۡرٞ مِّنۡ أَلۡفِ شَهۡرٖ ٣ تَنَزَّلُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ وَٱلرُّوحُ فِيهَا بِإِذۡنِ رَبِّهِم مِّن كُلِّ أَمۡرٖ ٤ سَلَٰمٌ هِيَ حَتَّىٰ مَطۡلَعِ ٱلۡفَجۡرِ ٥ ﴾

**ትርጉም (( እኛ (ቁርአኑን) በመወሰኛይቱ ሌሊት አወረድነው መወሰኛይቱም ሌሊት ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ ? መወሰኛይቱ ሌሊት ከሺህ ወር በላጭ ናት በርሷ ውስጥ መላእክትና መንፈሱ በጌታቸው ፈቃድ በነገሩ ሁሉ ይወርዳሉ እርሷ እስከ ጎህ መውጣት ድረስ ሰላም (የሰፈነባት ሌሊት) ብቻ ናት ))** አልቀድር 1 - 5

## አል ኢዕቲካፍ

**---ኢዕቲካፍ ማለት አላህን ለመገዛት (ለዒባዳ) ነይቶ ለተወሰነ ጊዜ መስጊድ ተጠቃሎ መግባት ማለት ነው ::**

# በረመዳን ፆም ዙርያ ጥያቄና መልስ

**1ኛ - ጥያቄ:- የረመዳን ወር በመግባቱ ሰበብ ሰዎች የተለያየ የብስራት ቃል ይለዋወጣሉ ይህም መረጃ አለውን ?**

**መልስ:- በረመዳን መግቢያ ብስራት መለዋወጥ ምንም አይደለም አላህም በቁርአኑ:-**

قال الله تعالى: {قُلْ بِفَضْلِ اللَّهِ وَبِرَحْمَتِهِ فَبِذَلِكَ فَلْيَفْرَحُواْ هُوَ خَيْرٌ مِّمَّا يَجْمَعُونَ}

**ትርጉሙ (( በአላህ ችሮታና በእዝነቱ (ይደሰቱ) በዚህም ምክንያት ይደሰቱ እርሱ ከሚሰበስቡት ሐብት በላጭ ነው በላቸው))** ዩኑስ / 58

أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: (أيها الناس! قد أظلكم شهر عظيم مبارك...)

**ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ሰዎች ሆይ የተባረከው ትልቁ ወር አጠለላቹህ.... » ይሉ ነበር**

**2ኛ - ጥያቄ:- ለምሳሌ ቅዳሜ ሳዑዲ ዐረቢያ ላይ ፆም የያዘ መንገደኛ አልጄሪያ ሲደርስ ፆም የተያዘው በአንድ ቀን ልዩነት እሁድ ቀን ቢሆን ይህ ተጓዥ ዒድ የሚያፈጥረው ከሳዑዲዎች ጋር ነው ወይንስ ከአልጄሪያዎች ጋር ነው ?**

**መልስ:-** قال النبي صلى الله عليه وسلم: (صوموا لرؤيته وأفطروا لرؤيته)

**ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «(ጨረቃን) አይታቹህ ፁሙ አይታቹህ አፍጥሩ» ስላሉ ጠያቂው ዒድ የሚያፈጥረው ባለበት ቦታ ከአልጄሪያዎች ጋር ነው ::**

**3ኛ - ጥያቄ:- ሁለት ሃገሮች በጨረቃ እይታ ሲለያዩ አንድ ሙስሊም ምን ማድረግ አለበት ?**

**መልስ:- የጨረቃ መውጫዋ ስለሚለያይ የሚኖርበትን ሃገር ሙስሊሞች ተከትሎ መፆም አለበት::**

**4ኛ - ጥያቄ:- ከጨረቃ እይታ ውጪ በቀን መቁጠሪያ ፆም መያዝ ይቻላል ?**

**መልስ:- ፆምን በቀን መቁጠርያ (ካላንደር) መያዝ አይፈቀድም ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «(ጨረቃን) አይታቹህ ፁሙ አይታቹህ አፍጥሩ» ይሉ ነበር**

قال النبي صلى الله عليه وسلم: (صوموا لرؤيته وأفطروا لرؤيته)

5ኛ - ጥያቄ:- የረመዳን ወር ከፈጅር በኋላ መግባቱን ያወቀ ሰው ምን ማድረግ አለበት ?

መልስ:- ከፈጅር በኋላ የረመዳን ወር መግባቱን ያወቀ ሰው ፆም መያዝ አይችልም ቀሪዎችን ቀን ፆሞ ያመለጠውን ቀን ቀዷ ማውጣት አለበት ምክንያቱም ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም)

قال صلى الله عليه وسلم: (لا صيام لمن لم يجمع الصوم من الليل)

«በሌሊት ኒያ አድርጎ ያላደረ ፆም የለውም) ብለዋል፡

ኢማም ማሊክ ሙወጣ ላይ አስፍረውታል

6ኛ - ጥያቄ:- በደመና ግርዶሽ ሰበብ ሙአዚን በስህተት መቅሪብ አዛን ብሎ ሰዎች ካፈጠሩ በኋላ ፀሐይን ቢያዩስ ?

መልስ:- (እኔ እንደማውቀውና ብዙ ዑለማዎች እንደሚሉት ፀሐይ ሳትጠልቅ ያፈጠረ ሰው ፆሙ ሙሉ ስላልሆነ ቀዷ ማውጣት አለበት) አላህም በቁርአኑ:

والله تعالى يقول: {ثُمَّ أَتِمُّواْ الصِّيَامَ إِلَى الَّليْلِ.} البقرة: آية 187].

ትርጉም ((...**ከዚያም ፆምን እስከ ሌሊቱ ድረስ ሙሉ** ...)) ይላል

በእርግጥ በስህተት ፀሐይ ሳትጠልቅ ያፈጠረ ሰሐባ ነበር እናም በቀዷ አልታዘዘም ይህንን ይዘው ቀዷ መውጣት የለበትም የሚሉ ቢኖሩም ቀዷ ማውጣቱ
የተሻለ ነው ።

7ኛ - ጥያቄ:- አንድ ፃሚ ፈጅር ማለፉን እና ያለማለፉን ሲጠራጠር ምን ማድረግ አለበት ?

መልስ:- መጀመርያ በደንብ ማረጋገጥ አለበት ፈጅር መድረሱን ማረጋገጥ ካልቻለ ጥርጣሬው ወደሚያመዝነው መወሰን ይችላል ምክንያቱም ጥርጣሬ ሚያመዝነው ለሃቅ የቀረበ ነው ይባላልና ማረጋገጡ ግን የተሸለ ነው :- ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ከማያጠራጥርህ የሚያጠራጥርህን ተው» ብለዋል

قال صلى الله عليه وسلم: (دع ما يريبك إلى ما لا يريبك)

8ኛ - ጥያቄ:- የፈጅርን አዛን እየሰማ መብላቱን ለማያቆም ፂሚ ሕጉ ምንድን ነው ?

መልስ:- ፈጅር መግባቱ ከተረጋገጠ ፆም መያዙ ግዴታ ነው ሙአዚን አዛን እያለ መብላት መጠጣት ክልክል ነው ፡ ሙአዚኑ ፈጅር ሳይገባ ተቻኩሎ አዛን የሚል ከሆነ መብላቱ ምንም አይደለም ::

## ፆም የሚያበላሹና በፆም ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ነገሮች

9ኛ - ጥያቄ:- ባጠቃላይ ፆም የሚያበላሹ ነገሮች ምን ምን ናቸው ?

መልስ:- ፆም የሚያበላሹ ነገሮች :-

ሀ -- እያወቁ መብላትና መጠጣት ::

ለ -- የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ::

ሐ --አውቆ ከብልት ፈሳሽ ማስወጣት ::

መ -- የአይን፣ የጆሮ፣ እና የአፍንጫ ጠብታ ተንሸራቶ ወደ ጉሮሮ መግባት ::

ሠ -- እንደ ግሉኮዝ አይነትና ምግብ ነክ መርፌ መውሰድ::

ረ -- ዋግምት ማድረግ ::

ሸ - በወር አበባና በወሊድ ደም ወቅት:: ( መፆሙ ሐራም ነው )

ቀ -- አውቆ ማስታወክ ናቸው :: (ገፍቶ የመጣ ትውከት ፣ ረስቶ መብላትና መጠጣት ፆም አያበላሹም )

10ኛ - ጥያቄ:- የአይን ኩሁል ሽቶ ኮስሞቲክ የመሳሰሉት ለፆመኛ ይፈቀዳል ወይ?

መልስ:- ኩሁል አይን ላይ ሲኳሉት ወደ ጉሮሮ ይዘልቃል ስለዚህ ብዙ የዲን ዕውቀት ባለቤቶች ከልክለዋል ፓውደር ሽቶ የመሳሰሉት ለፆመኛ ምንም አይደለም ሴቶች ግን ሽቶ ተቀብተው ከቤት መውጣታቸው ሐራም ነው ፡ ሴቶች ከቤታቸው ውጪ ሲወጡ ከማጋጌጥና ሽቶ ከመቀባት መራቅ አለባቸው አላህም በቁርአኑ :-

قال تعالى: {..وَلا تَبَرَّجْنَ تَبَرُّجَ الْجَاهِلِيَّةِ الأُولَى ...}

**ትርጉሙ ((...እንደፊተኛይቱ መሃይምነት ጊዜ መገለጥን በማጌጥ አትገለጡ...)) ይላል::** አል አሕዛብ / 33

**قال صلى الله عليه وسلم: (لا تمنعوا إماء الله مساجد الله وليخرجن تَفِلات)**

**-- ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «ሴት የአላህ ባሮችን መስጊድ አትከልክሉ ያላጌጡም ሆነው ይውጡ) ብለዋል::** አቡ ዳውድ ሱነን ላይ

**11ኛ - ጥያቄ:- ፆመኛ በአደጋም ሆነ በጭረት ከሰውነቱ ደም ቢፈስ ፆሙ ይበላሻል ?**

**መልስ:- በአደጋ ምክንያት የሚፈስ ደም በፍላጎት ስላልሆነ ፆም አያጠፋም :: ደም መስጠትና ዋግምት ግን ስለሚያደክምና ስለሚያስፈጥር በፆም ወቅት ክልክል ነው ::**

**12ኛ - ጥያቄ:- በየፋርማሲው የሚሸጥ የአፍ ሽታ የሚያጠፋ የሚነፋ ፈሳሽ (ስፕሬይ) ፆም ያበላሻል ?**

**መልስ:- ፈሳሹን ለአፍ መጠቀም እንደመፋቂያ ስለሆነ ይቻላል ወደ ጉሮሮ ዘልቆ እንዳይገባ መጠንቀቅ ያስፈልጋል :: እዚህ ላይ ፆመኛ የአፉን ጠረን በጣም መጥላት የለበትም ምክንያቱም አላህን የመታዘዝ ምልክትና የተወደደም ነውና ::**

قال صلى الله عليه وسلم : **(خلوف فم الصائم أطيب عند الله من ريح المسك)**

**ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «የፆመኛ የአፍ ጠረን አላህ ዘንድ ከምስክ ሽቶ የተሸለ ነው) ብለዋል::** ቡኻሪ እንደዘገበው

**13ኛ - ጥያቄ:- አንዲት ሴት ከወር አበባ ወይንም ከወሊድ ደም ከጠራች በኋላ የሚያጠራጥር ነገር ካየች እንዴት ትሆናለች ?**

**መልስ:- የወር አበባ ባስለመደው ቀን ጊዜውን ጨርሶ ምልክት አሳይቶ ከቆመ በኋላ መስገድም ሆነ መፆም ትችላለች ምናልባት የሚያጠራጥር ነገር ካየች ያለማወላወል ፆሚን መቀጠልም ሆነ መስገድ ትችላለች ነገር ግን ከወሊድ ደም ጠርቻለሁ ካለች በኋላ የሚያጠራጥር ነገር ካየች የግድ አርባ ቀን መሙላት አለባት ከአርባ ቀን በኋላ አጠራጣሪ ነገር ብታይም ሳታወላውል ፆሚን መቀጠልም ሆነ መስገድ ትችላለች::**

**أم عطية رضي الله عنها: (كنا لا نعد الكدرة والصفرة بعد الطهر شيئًا)**

-- ኡሙ ዓጢያ (ረዲየሏሁ ዓንሃ) (ከወር አበባ ከጠራን በኋላ አረንጓዴውን ፈሳሽ (ኩድራ) እና ቢጫውን ፈሳሽ (ሱፍራን) እንደ ወር አበባ አንቆጥረውም ነበር ) ብላለች

14ኛ - ጥያቄ:- የአሥራ አራት አመት ኮረዳ እያለሁኝ የወር አበባ ታየኝ በዛኑ አመት ረመዳን ሲመጣ አልፃምኩም መፃም እንደሚገባኝ እኔም ሆንኩኝ ቤተሰቦቼ አናውቅም አሥራ አምስት አመት ሲሞላኝ መፃም ጀመርኩኝ ከዛም ሴት ልጅ የወር አበባ ከታያት ዕድሜዋ ባይደርስም መፃም አለባት የሚል ፈትዋ ሰማሁኝ ታድያ አሁን ምን ላድርግ ?

መልስ:- ጠያቂዋ የወር አበባ ሲታያት ለአካለ መጠን መድረሷን ባለማወቋ እንደ ጥፋት አይቆጠርም ያለማወቅ ነውና ስለዚህ አሁን ለአካለ መጠን ስለደረሰች ያልፃመችውን አመት ፃም ቀዷ ማውጣት አለባት ::

ሴት ልጅ ለአካለ መጠን መድረሷ የሚታወቅበት አራት ነጥቦች አሉ::

ሀ - ዕድሜዋ አሥራ አምስት አመት ሲሞላት ::

ለ -- ፀጉር ስታበቅል (ብልት አካባቢ)

ሐ -- በስሜት ማፍሰስ ስትጀምር (በብልት በኩል)

መ -- የወር አበባ ሲታያት ናቸው ::

ከአራቱ አንዱ ከተከሰተ ሴት ልጅ ልክ እንደ ትልቅ ሴት ግዴታ የሆኑ ዒባዳዎችን ሁሉ መፈፀም አለባት ::

15ኛ - ጥያቄ:- ያለፉትን ብዙ ረመዳኖች ለዓመታት አልፃምኩም አሁን ተውበት አድርጌ በደንብ መፃም ከጀመርኩኝ ገና ዓመቴ ነው ታድያ ያለፉትን ዓመታት ቀዷ እንዴት ነው የማወጣው ?

መልስ:- ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ትንታኔ ያስፈልገዋል ያለፉትን ሳትፃም ያሳለፍካቸው ረመዳኖች በዛን ወቅት ሰላት የማትሰግድ ከሆነ ከኢስላም ውጪ ስለሆንክ ብትፃምም ፃምህ ተቀባይነት የለውም ነገር ግን ባለፉት ባልፃምክባቸው ረመዳኖች ዘመን ሰላትህን አስተካክለህ የምትሰግድ ከሆነ ያልፃምካቸውን ረመዳኖች ሁሉ ቀዷ ማውጣት አለብህ ቀዷ ስታወጣ ቀዷውን ያዘገየህበት ምክንያት ከሌለህ

በያንዳንዱ ቀን ምስኪን ማብላት አለብህ ቀዷውን በምክንያት ካዘገየህ ምስኪን ባታበላም ምንም አይደለም ::

***16ኛ - ጥያቄ:- ፈርድ የሆነ ፆም ቀዷ በማውጣት ላይ ያለ ሰው ቀን ላይ ፆሙን ማቋረጥ ይችላል ? የሱና ፆም (ነፍል) ቢሆንስ ?***

*መልስ:-* ፈርድ የሆነ ፆም ቀዷ በመፆም ላይ ያለ ሰው ፆሙን ማቋረጥ አይችልም ፈርድ ነውና ነገርግን የሱና ፆም (ነፍል) ከሆነ ቀን ላይ ከፈለገ ማቋረጥ ይችላል ::

***17ኛ - ጥያቄ:- እናቴ የስልሳ አመት አዛውንት ናት አባቴን ካገባች ጀምሮ በወር አበባ ሰበብ ያልፆመቻቸውን ፆሞች ለሃያ ዓመት ቀዳ አላወጣችም ምክንያቱ አባቴ ከፋራ ካደረግሽ በቂ ነው ይላት ነበር አሁን ታድያ ምን ማድረግ አለባት :: ?***

*መልስ:-* እናትህ በወር አበባ ሰበብ ያልፆሙትን ቀን በሙሉ መፆም አለባቸው እንዲያውም ቀዳውን ስላዘገዩ በያንዳንዱ ቀን ምስኪን ማብላት አለባቸው :: አባትህን በተመለከተ በማያውቁት ነገር ፈትዋ መስጠታቸው ትልቅ ስህተት ተሳስተዋል ::

***18ኛ - ጥያቄ:- አንድ ሰው በሕመም ምክንያት ሐኪም ከልክሎት የአራት ዓመት ረመዳኖችን አልፆመም አሁን ጤንነቱ ስለተሟላ ምን ማድረግ አለበት ?***

*መልስ:-* በሕመም ምክንያት ያሳለፋቸው ፆሞች ጤናው ከተመለሰ ቀዷ ማውጣት ግዴታው ነው አላህም በቁርአኑ :-

والله تعالى يقول: {....وَمَن كَانَ مَرِيضًا أَوْ عَلَى سَفَرٍ فَعِدَّةٌ مِّنْ أَيَّامٍ أُخَرَ}

**ትርጉም ((ከናንተ ውስጥ በሽተኛ ወይንም በጉዞ ላይ የሆነ ሰው ከሌሎች ቀኖች የተወሰነውን *መፆም* አለበት .... ))** አል በቀራህ 185

ቀዳ ሲወጣ ግን እንደፈለጉ አከታትሎም ሆነ አቆራርጦ መፆም ይቻላል አላህ ከአቅም በላይ አያዝም በቁርአኑም {فَاتَّقُوا اللَّهَ مَ اسْتَطَعْتُمْ .}

**ትርጉም ((አላህንም የቻላችሁትን ያክል ፍሩት.))ይላል** አል ተጋቡን/ 16

*19ኛ - ጥያቄ:- እናቴ አላህ ይማራትና ከመሞቷ በፊት በጭንቅላቷ ወድቃ አዕምሮዋ ስለተነካ ለአንድ አመት ያክል ሰላትም ሆነ ፆም አትችልም ነበር አሁን እኔ ልጇ ምን ላድርግላት ?*

*መልስ:- እናትህ እንደምትለው አዕምሮዋ ከተነካ ፆም ግዴታ አይሆንባትም ነበር ግን አዕምሮዋ ጤነኛ ከሆነና ከተወችው ከውርስ ንብረት ላይ ተወስዶ ከፋራ መከፈል አለበት የተወችው ንብረት ከሌለ ከቤተሰብ አንዱ ቢከፍልላትም ሆነ ቢያምላት ሊጠቅማት ይችላል ::*

*20ኛ - ጥያቄ :- እድሜው አሥራ ስድስት አመት የሞላው ተማሪ በረመዳን ፆም የትምህርት ቤት ፈተና ቢገጥመው ለፈተናው እንዲመቸው ብሎ ማፍጠር ይችላል ?*

*መልስ :- ለአካለ መጠን የደረሰ ተማሪ በፈተና ሰበብ ማፍጠር አይችልም አላህ በቁርአኑ :-* {فَمَن شَهِدَ مِنكُمُ الشَّهْرَ فَلْيَصُمْهُ ...}

*ትርጉም ((* ***ከናንተ ውስጥ ወሩን ያገኘ ይፁም ..*** *))* *በቀራህ -185*

*ስለዚህ ካለሕመም በስተቀር በሌላ ምክንያት ፆምን መተው አይቻልም ለአካለ መጠን ያልደረሱ ሕፃናት ግን ቢያፈጥሩ ምንም አይደለም ::*

*21ኛ - ጥያቄ :- አራት መቶ ኪሎ ሜትር የሚጓዝ መንገደኛ ማፍጠር ይችላል ? የሚችል ከሆነ ስንት ቀን ድረስ ነው የሚያፈጥረው ?*

*መልስ :- መንገደኛ የሚጓዘው ከሰማንያ ኪሎ ሜትር በላይ ከሆነ ማፍጠርም ሆነ ሰላትን አሳጥሮ መስገድ ይችላል መንገደኛው የሚመለስበትን ቀን የማያውቀው ከሆነ ላልተወሰነ ጊዜ ፆሙን ማፍጠርም ሆነ ሰላቱን ማሳጠር ይችላል : የተጓዘበት አካባቢ ሲደርስ እዛው ለመኖር ከነየተ ከአራት ቀንና ሌሊት በላይ ማፍጠርም ሆነ ሰላት ማሳጠር አይችልም*

*22 - ጥያቄ :- እባኮትን እስኪ ስለረመዳ የመጨረሻ አስር ቀኖች (ዓሽረል አዋኺር) ጥቅምና ደረጃውን ቢያብራሩልን ?*

*መልስ :- የዓሽረል አዋኺር ደረጃው በጣም ትልቅ ነው*

--- ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በረመዳን ከመጀመርያዎቹ ቀኖች ይበልጥ በዓሸረል አዋኺር በዒባዳ ይጥራሉ፣ ተሐጁድ ሰላት ይሰግዳሉ፣ ኢዕቲካፍ ለማድረግ መስጊድ ተጠቃለው ይገባሉ ፣ ለይለተል ቀድርንም ለማግኘት በዓሸረል አዋኺር በይበልጥ ተስፋ ያደርጋሉ ፡፡

23 - ጥያቄ ፡- በተባረከው የረመዳን ወር የተወደዱት ሥራዎች የትኞቹ ናቸው ?

መልስ ፡- በረመዳን የተወደዱ ሥራዎች በጣም ብዙ ናቸው ከነሱም ውስጥ አላህ ግዴታ ያደረጋቸውን ሰላትም ሆነ ፆም በትክክል መፈፀም:

ግዴታ ያልሆኑ ተጨማሪ ሥራዎችን ማብዛት ይኸውም ቁርአን መቅራት ፣ ተራዊሕ እና ተሃጁድ መስገድ፣ ሰደቃ መስጠት፣ ኢዕቲካፍ መግባት ፣ አላህን ማውሳት ማብዛት፣ ለዒባዳ ብሎ መስጊድ መቀመጥ ማብዛት፣ ከተጠሉና ከተከለከሉ ሥራዎችና ቃሎችን መቆጠብ እና ፆም እንዳይበላሽ መጠንቀቅ ናቸው ፡፡

24ኛ - ጥያቄ ፡- ኢዕቲካፈ ምን ማለት ነው ? ደንቡስ እንዴት ነው ? ቤቴ ውስጥ ኢዕቲካፍ ማድረግ እችላለሁ ?

መልስ ፡- ኢዕቲካፍ በኢስላም ትልቅ ዒባዳ ነው አላህም በቁርአኑ ለነብዩ ኢብራሂምና ኢስማዒል (አለይሂማ ሰለም) እንዲህ ብሏቸዋል፡-

قال تعالى: ﴿ وَإِذْ بَوَّأْنَا لِإِبْرَٰهِيمَ مَكَانَ ٱلْبَيْتِ أَن لَّا تُشْرِكْ بِى شَيْـًٔا وَطَهِّرْ بَيْتِىَ لِلطَّآئِفِينَ وَٱلْقَآئِمِينَ وَٱلرُّكَّعِ ٱلسُّجُودِ ﴿٢٦﴾ ﴾

ትርጉም (( **ለኢብራሂም የቤቱን (የከዕባን) ስፍራ መመለሻ ባደረግንለት ጊዜ በኔ ምንንም አታጋራ ቤቴንም ለሚዞሩትና ለሚቆሙበት ለሚያጎነብሱትና በግንባራቸው ለሚደፉት ንፁሕ አድርግላቸው /ባልነው ጊዜ አስታውስ/** )) አል ሐጅ / 26

ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በረመዳን ግማሽ ጀምሮ ኢዕቲካፍ ይገቡ ነበር በሕይወታቸው መጨረሻ አካባቢ ለይለቱል ቀድር ይበልጥ ተስፋ የሚደረገው በዓሸረል አዋኺር ሊሆን እንደሚችል ሲገለፅላቸው በረመዳን በመጨረሻ አስሩ ቀኖች ኢዕቲካፍ ለማድረግ ከነባለቤቶቻቸው መስጊድ ይገቡ ጀመር ፡፡

ኢዕቲካፍ ከመስጊድ በስተቀር ቤትም ሆነ ሌላ ቦታ አይቻልም አላህም በቁርአኑ ፡-

قال تعالى: ﴿.... وَلَا تُبَٰشِرُوهُنَّ وَأَنتُمۡ عَٰكِفُونَ فِي ٱلۡمَسَٰجِدِ..... ١٨٧﴾

**ትርጉም (( እናንተም በመስጊዶች ተቀማጮች ስትሆኑ /ሴቶችን/ አትገናኙዋቸው)) ይላል**

***25ኛ- ጥያቄ -: በረመዳን ቀኑን ሙሉ ተኝቶ በማፍጠርያ ሰዓት ከንቅልፉ የሚነሳ ሰው እንዴት ይታያል (ሁክሙ) ምንድነው ?***

*መልስ:- ከፈጅር በፊት ፆም ነይቶ ቀኑን ሙሉ የተኛ ፂሚ ፆሙ ትክክል ነው ነገር ግን በሰላቶች ወቅት መተኛቱ ሐራም ነው መጀመርያ ሰላቱን በወቅቱ ያለመስገዱ ሁለተኛ ጀማዓ ሰላት መስጊድ ያለመሄዱ ሲደመርበት ትልቅ ወንጀል ሰራ ማለት ነው ። በዚህ አጋጣሚ በጣም የሚያሳዝነኝ ጉዳይ ብዙ ሰዎች ልምድ አድርገው የያዙት በረመዳን ሌሊቱን በማይረባ ነገር አምሽተው ፈጅር ሲደርስ ሱሑር በልተው ቀኑን ሙሉ ይተኛሉ ፆም ደግሞ ያለሰላት ተቀባይነት የለውም ስለዚህ እንደነዚህ አይነት ሰዎች አደጋ ላይ ነው ያሉት ማለት ይቻላል።*

*በመጨረሻ በረመዳን ፆም ዙርያ የተዘጋጀው ትርጉም ሥራ በዚህ ይጠናቀቃል ። ባነበብነው ተጠቅመን ፆማቸውን ከሚቀበላቸው ባሮቹ  አላህ ያድርገን ።*

*አሚን ///*

# فهم الشهادتين

هل يفهم من تلك الشهادتين أن للرسول صلى الله عليه وسلم حقوقًا توازي حق الله سبحانه وتعالى كما يتوهم بعض من يدعي محبة رسول الله صلى الله عليه وسلم؟ وإذا لم يفهم ذلك؛ فما هي الحقوق الخاصة بالله سبحانه وتعالى؟ وما هي الحقوق الخاصة بالنبي صلى الله عليه وسلم؟ وهي هناك حقوق مشتركة لا شك أن للرسول صلى الله عليه وسلم حقوقًا خاصة به، لكنها لا ترقى إلى مرتبة حقوق الله؛ لأن حقوق الله تعالى لا يشاركه فيها أحد؛ لا ملك مقرب، ولا نبي مرسل، ولا ولي من الأولياء، أو صالح من الصالحين.

ولهذا يقول ابن القيم رحمه الله:

لله حق لا يكون لعبده ** ولعبده حق هما حقان

لا تجعلوا الحقين حقًا واحدًا ** من غير تمييز ولا برهان (1)

فحق الله تعالى عبادته وحده لا شريك له بما شرعه، وحق الرسول صلى الله عليه وسلم محبته وطاعته وتوقيره واتباعه وتقديم أمره وطاعته على طاعة غيره من المخلوقين.

وليس هناك حق مشترك بين الله وبين رسوله، وقوله تعالى: {مَّنْ يُطِعِ الرَّسُولَ فَقَدْ أَطَاعَ اللَّهَ} [النساء:80]؛ لأن طاعة الرسول طاعة لله الذي أرسله؛ كما أن مبايعة الرسول مبايعة لله؛ قال تعالى: {إِنَّ الَّذِينَ يُبَايِعُونَكَ إِنَّمَا يُبَايِعُونَ اللَّهَ} [الفتح:10]؛ فأصل الطاعة لله عز وجل، وطاعة الرسول صلى الله عليه وسلم تابعة لطاعة الله عز وجل.

# فضل ليلة القدر

ـــ يرجى بيان فضل ليلة القدر، وما ورد فيها من الآيات الكريمات؟

نوَّه الله تعالى بشأنها، وسماها ليلة القدر: قيل: لأنها تقدَّر فيها الآجال والأرزاق وما يكون في السنة من التدابير الإلهية؛ كما قال تعالى: {فِيهَا يُفْرَقُ كُلُّ أَمْرٍ حَكِيمٍ} [سورة الدخان: آية 4]، فسماها الله

ليلة القدر من أجل ذلك. وقيل: سميت ليلة القدر لأنها ذات قدر وقيمة ومنزلة عند الله سبحانه وتعالى.

وسماها ليلة مباركة؛ كما قال تعالى: {إِنَّا أَنزَلْنَاهُ فِي لَيْلَةٍ مُّبَارَكَةٍ إِنَّا كُنَّا مُنذِرِينَ} [ الدخان: آية 3].

ونوه الله بشأنها بقوله: {وَمَا أَدْرَاكَ مَا لَيْلَةُ الْقَدْرِ، لَيْلَةُ الْقَدْرِ خَيْرٌ مِّنْ أَلْفِ شَهْرٍ} [سورة القدر: آية 2، 3]؛ أي: العمل في هذه الليلة المباركة يعدل ثواب العمل في ألف شهر ليس فيها ليلة القدر، وألف شهر ثلاثة وثمانون عامًا وزيادة؛ فهذا مما يدل على فضل هذه الليلة العظيمة.

ولهذا كان النبي صلى الله عليه وسلم يتحراها ويقول صلى الله عليه وسلم: (من قام ليلة القدر إيمانًا واحتسابًا؛ غفر له ما تقدم من ذنبه وما تأخر) [رواه البخاري في صحيحه (253/2). (بدون ذكر... وما تأخر) ].

وأخبر سبحانه وتعالى أنها تنزل فيها الملائكة والروح، وهذا يدل على عظم شأنها وأهميتها؛ لأن نزول الملائكة لا يكون إلا لأمر عظيم.

ثم وصفها بقوله: {سَلامٌ هِيَ حَتَّى مَطْلَعِ الْفَجْرِ} [سورة القدر: آية 5]، فوصفها بأنها سلام، وهذا يدل على شرفها وخيرها وبركتها، وأن من حرم خيرها؛ فقد حرم الخير الكثير.

فهذه فضائل عظيمة لهذه الليلة المباركة. ولكن الله بحكمته أخفاها في شهر رمضان؛ لأجل أن يجتهد المسلم في كل ليالي رمضان؛ طلبًا لهذه الليلة، فيكثر عمله، ويجمع بين كثرة العمل في سائر ليالي رمضان مع مصادفة ليلة القدر بفضائلها وكرائمها وثوابها، فيكون جمع بين الحسنيين، وهذا من كرم الله سبحانه وتعالى على عباده.

وصلى الله على نبينا محمد وعلى آله وصحبه وسلم تسليماً كثيراً .